ኮንፊሺየስ እና ፍልስፍናው

/ ክፍል ፰ /

□□□□

ኮንፊሺየስ ከክርስቶስ ልደት በፊት በተለይም በነቢዩ ሕዝቅኤልና በቡድሃ ዘመን የኖረ ሰው እንደነበር ታሪክ ይነግረናል ። የኮንፊሺየስ ፍልስፍና በአብዛኛውና በዋናነት "ሰብዓዊነት" ነው ። በተለይም የሞራልን ጉዳይ በሰው ተፈጥሮ ውስጥ አልቆ ማሳየት ዋነኛ ግቡ ያደርገዋል ። የግሪኩ ፍልስፍና "ግብረ ገብነት ከልምድ ወይም ባህል ይመጣል" ሲል ኮንፊሺየስ ግን " ግብረ ገብነት መሰረቱ ሰው ነው " ይለናል ። ለዚህም ነው ለቻይናውያን የሞራል ጉዳይ ባለበት ሁሉ ምልክቱ "ልብ" የሆነው ። ኮንፊሺየስ ስለዚህ ጉዳይ ሲያስረዳን " የማንኛውም ነገር ሥሩ የሰውን ልጅ መኮትኮት ነው ። የፍልስፍናም ተግባር የሰው ልጅ እንዴት እርባና ሊኖረው እንደሚችል ማስተማር ሲሆን የትምህርቱ መሰረት ደግሞ ወደ ምድር ወርዶ የሰውን ተፈጥሮ በማሳየት ላይ ሊመሰረት ይገባል " ይለናል ።

□□□

የሰው ልጅ ሊያንፀውና ሊኮተኩተው የሚገባ ትልቁ ነገር ደግሞ ቢኖር "ልቡን" ነው ፤ እነኮንፊሽየስ ዩን(Jen) ይሉታል ። ይኽ የኮንፊሺየስ እሳቤ (ልብን ማነፅ) በአይሁድ ፃድቅነትን ፣ በክርስትና ለጋስነትን ፣ በቡድሃ ደግሞ ከራስ መላቀቅ እንደሚባለው ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል ። አንድ ወቅት ኮንፊሺየስ "መልካም ተግባር ምንድነው?" በማለት ተማሪዎቹ ሲጠይቁት ፦ " ወንድምህን መውደድ ነው " አላቸው ። " እውቀትንስ ምንድነው? " አሉት " እውቀት ደግሞ ወንድምህን ማወቅ! " አላቸው ። ሰው ሁሉን ነገር ነው ። ዩን ደግሞ ሙሉ ሰው መሆንን ይጠይቃል ። በአጭሩ ሰብአዊነት አድርገን የምንወስደው #ዩን በውስጡ እጅግ የበዛ ምህረትና ፍቅር የተሸከመ በመሆኑ ከተራ ሰብዓዊነት በእጅጉ እንደሚለይ ኮንፊሺየስ ይነግረናል ።

□□□

<< የመልካም ሰው መፍለቂያ መልካም ማኅበረሰብ ነው ፤ አንድ ሰው ከምንም በላይ አስፈላጊነቱ ለማኅበረሰቡ በመሆኑ ሰው ከራሱ ሕይወት ይልቅ በማኅበረሰቡ ላይ የሚጫወተው ሚና የላቀ ነው ። ይሁንና በቻይና እንዲህ አይነቱ ነገር የተገላቢጦሽ ይታያል >> የሚለው ኮንፊሺየስ <<ሚናውን ከግለሰቡ ጋር እንጂ ከማኅባረሰቡ ጋር የሚያቆራኝ አስተሳሰብ የለንም ...ቀዳሚ ሊሆን የሚገባው ግለሰቡ እንጂ የያዘው ሥልጣን መሆን የለበትም ፤ ምክንያቱም ሥልጣኑን የሚከውነው ግለሰቡ ነውና ። ቁምነገሩ በመንግሥት ውስጥ ያለው ሕግ ሳይሆን በመንግስት ውስጥ ያሉት ግለሰቦች ማንነት ነው ።....>> ይላል ።

□□□

"..አድልዎንና በስልጣን አላግባብ መገልገልን ስናወግዝ በባለስልጣናቱ ልብ ውስጥ #ዩን ምን ያህል አለ? የሚለውንም አብረን እየጠየቅን መሆኑ ሊታወቅ ይገባል ። የሰው ልጅ በልቡ ውስጥ የተቀመጠውን ካልነገ በቀር የማይገባውን ይፈፅም ዘንድ የግድ ነውና..." ይለናል...

ይቀጥላል ...

ኮንፊሽየስ እና ፍልስፍናው

/ ክፍል ፪ /

□□□□

ኮንፊሺየስ << ሞራላዊና መንፈሳዊ እሴቶቻችን ከገነት የሚወርዱ እንጂ ከምድር የሚፈልቁ አይመስሉንም ፤ የምናፀናቸውም በእምነት እንጂ በማሰብ አይደለም ። ታዲያ ጥያቄው የሰውን ልጅ ሳታገለግል ፈጣሪን እንዴት ታገለግላለህ? የሚለው ይሆናል >> ይለናል ።

⁞

ኮንፊሺየስ እንደቡድሀ ሁሉ በተዓምራትና በአምላካዊ ኃይል ላይ ውይይት ማድረግ አይፈልግም ፤ ምክንያቱንም ሲናገር ፦ << የምንነጋገርበት ነጥብ ሳይኖር እንዴት መግባባት እንችላለን? >> በማለት ነው ።

□□□

ኮንፊሺየስ አያይዞ ይጠይቃል ፦ " ሕይወትን ጠንቅቀህ ሳትረዳ ስለሞት እንዴት ይገባሃል? የመጀመርያውን መጀመርያ መመለስ አይገባምን? " ይላል ። ኮንፊሺየስ በአስተሳሰቡ የገነትን ስፍራ የሚያስቀምጠው በዕለት ተዕለት ሥራችን ውስጥ ነው ፦ " የገነትን መንገድ የተረጋገጠና ከእኔ በላይ የሚገኝ ነው ማለትን አልሻም ፤ ነገር ግን እንደየዕለቱ ሥራዬ አንዳንድ ጊዜ ከእኔ በላይ በሌላ ዝቅ ደግሞ ከእኔ በታች ይውላል " ብሏል ።

⁞

ይኽ ዓይነቱ አስተሳሰብ ግን የመንፈስን ነገር ፈፅሞ እንደማጣጣል ሊቆጠር እንደማይገባ የሚነግሩን ፈላስፎች አሉ ። ቻይናውያን በተግባራዊ ሕይወት ያምናሉ ። ኮንፊሺየስ " ይኽ አስተሳሰብ በተጨናነቀውና በአስጨናቂው የቻይና ባህር ላይ ሁለት እግሮችን በሁለት ጀልባ ላይ አድርጎ እንደመቅዘፍ ቢሆንም በዚያው መቀጠል ግን እሻለሁ " ይላል ። ስለዚህም የኮንፊሺየስ የሞራል ትርጉም በእውነት ላይ እንጂ በእምነት ላይ የተመሰረተ አይደለም ።

□□□

" የሰው ልጅ በሕይወቱ ውስጥ በሚያደርገው የሞራል ጉዞ ሊመለከት የሚገባው የሚደርስበትን ከፍታ ወይም የሚወርድበትን ዝቅታ ሳይሆን የሚጀምርበትን ቦታ ነው ። አሁን የትና ምን እየሠራሁ ነው ለሚለው ጥያቄ ምላሽን ካገኘ ጉዞውን ሳይጀምር መድረሻውን ያውቀዋል ለዚህም ነው የተግባር መንገድ ሁልጊዜ ቅርብ ነው የምንለው " ይለናል ኮንፊሺየስ ሲያብራራው ።

" የተግባር መንገድ ሁልጊዜ ቅርብ ሲሆን የሰው ልጅ ግን በሩቅ ያለውን ይሻል ፤ የሰው ልጅ ሕይወት በተግባር የሚሰራባት ስታገኝ ቀላል ስትሆን ፣ ነገር ግን ሰው የሚሻው ሩቁንና አስቸጋሪውን ነው ። ለዚህም ነው መልካም ተግባርን በዕምነት ለዓመታት ስፈልጋት መኖሬ ከንቱ መሆኑን ያወቅሁት ለካስ እኔው ዘንድ ትኖር ኖሯል " ይለናል ።

⁞

ኮንፊሺየስ ሲናገር ፦ " ሞራል በሕይወት ውስጥ ለምን እንደማትተገበር አሁን ተረዳሁ ፤ ጠቢባኑ የሞራልን ሕግ ከእውነታው ይልቅ አልቀው ያስቀምጡታል ፤ ሕዝቡ ደግሞ ሞራል የሚሉትን ነገር ፈጽሞ አያውቀውም ። ጥቂቶች ከሚነገራቸው የሞራል እሴት በላይ ጠብቀው ለመኖር ወደ ከፍታው ሲወጡ አያለሁ ፤ ብዙዎቹ ግን ከተራ ሞራል እሴቶቻቸው እንኳን ጥቂቱን አያውቁም ። በአጭሩ የሰው ልጅ መብላትና መጠጣት ያውቃል ፣ ማጣጣም የሚያውቁ ግን ጥቂቶች ናቸው " ይላል ። በዚህ አስተሳሰቡ ኮንፊሺየስ ከቡድሃና ከምዕራቡ ፍልስፍናዊ አስተሳሰብ ጋር የሚጋራው አለ ። ይኽንን አስተሳሰብ የምታሳይልን አንድ ወግ አለች ።

□□□

አንድ ቀን ኮንፊሺየስ ከተማሪዎቹ ጋር በደጃፍ ቁጭ ብሎ ሥለመልካም ተግባር ሲያስተምራቸው አንድ በድርጊቱ በአካባቢው ነዋሪ ዘንድ የተጠላ መስፍን የተዋበች ቆንጆ ሴት ይዞ ሲያልፍ ያስተውላል ። ተማሪዎቹ በሴቲቱ ቁንጅና እንዲት እንደተሳቡ ያስተዋለው ኮንፊሺየስ ፦ " ሴትን ልጅ የሚያፈቅረውን ያህል መልካም ተግባርን የሚያፈቅር ወንድ እስከዛሬ አይቼ አላውቅም " አላቸው ።...

ይቀጥላል ....

ኮንፊሸየስ እና ፍልስፍናው

/ ክፍል ፫ /

□□□□

መልካም ተግባር የምንላቸው ድርጊቶች " በአድርግና አታድርግ ትዕዛዝት የሚወሰኑ መሆን እንደሌለባቸው የሚነግረን ኮንፊሺየስ በማኅበረሰቡ ውስጥ መልካም ተብለው የሚታመኑ ድርጊቶች ተጠብቀው ሊኖሩ እንደሚገባም ያሳስባል ። በሌላም በኩል ደግሞ በሰው ልጅ የታሪክ ሂደት ውስጥ የተገኙ መልካም ተግባራት እንዲሁ ሊከወኑ እንደሚገባም ይመክራል ። በጥልቅ ሃሳቡን ስናይ " ነገሮችን ሁሉ የምናደርገው ከልምድ ባገኘነው ትምህርት ተመስርተን ነው " የሚል አስተሳሰብ ያስተላልፍልናል ። ለዚህም ነው ፦

" ለክፋት ደግነት መመለስ ተገቢ አይደለምን? " ተብሎ በተማሪው የተጠየቀው ኮንፊሺየስ

" ለክፋት ደግነትን ምላሽ ከሰጠህው ለደግነትስ ምላሹ ምን ይሆናል? " በማለት የመለሰለት ።

□□□

" በአሁን ጊዜ ቅዱስ ሰው ብሎ ሌላውን መጥራት በዓለም ሊኖር የማይችልን ነገር እንደመናገር እቆጥረዋለሁ፤ ይልቁንስ አንድ መልካም ሰው ካገኘሁ ለኔ ከበቂ በላይ ነው " የሚለው ኮንፊሺየስ በዘመኑ ሁሉ የቻይናን ፍልስፍናና ጥበብ በሰው ልጅ ሞራል ላይ በመመሥረት ወደ ከፍተኛ ደረጃ የወሰደው ነው እየተባለ ይነገርለታል ።

⁞

ለኮንፊሺየስ የሰብዓዊነት መሠረቱ ሰው ከአምላኩ ጋር ወይም ሰው ከሌላ መንፈሳዊ አካል ጋር በሚያደርገው ቁርኝትና ልመና የማይመሰረት መሆኑ ነው ። " የመልካም ተግባር መሰረቱ አክብሮት ነው ፤ ከዚያ ደግሞ የሞራል አስተምህሮት ይመነጫል ። ይኽ የሞራል አስተምህሮት ወላጅን በማገልገል ይጀመራል ፤ ከዚያም ለገዢዎች በመታዘዝ ይቀጥላል ፤ በመጨረሻም ባህርይን በማጽናት ይጠቃለላል " ይላል ።ይኽ ደግሞ በምዕራባውያኑ የፍልስፍና እሳቤ ሲተነተን " አንድ ሰው መጀመርያ ጥሩ ልጅ መሆን አለበት ፤ ከዚያም ጥሩ ዜጋ ይወጣዋል ፤ ቀጥሎም ጥሩ አባት ፤ በመጨረሻም ጥሩ ሰራተኛና መልካም መሪ ይሆናል " እንደማለት ነው ። " "ስለዚህም << ሰብዓዊ ልባዊነት >> የሚባለው የመልካም ተግባራት ሁሉ መሠረት የሆነው መገኛው ቤተሰብ ነው ።

□□□

የኮንፊሺየስን አስተሳሰብ በዚህ እንጠቀልለዋለን ፦

" የሰው ልጅ መልካሙን የአዕምሮ ባህርይውን የሚያጣበት መንገድ ልክ በመጥረቢያ የሚቆረጥ ዛፍ ጋር የሚመሳሰል ነው ። ዕለት ዕለት አስተሳሰብህን እንደዛፍ ቅርንጫፍ አየቆረጥህ ብትጥል ተፈጥሮአዊ ውበትህ እንደሚጠፋ ልብ ብለሃል? ነገር ግን ቀንም ሆነ ማታ የተቆረጠ ዛፍ ከማቆጥቆጥ እንደማይቆጠብ ሁሉ እንዲሁ ደግሞ የሰው አዕምሮ ወደነበረበት ለመመለስ መፀፀቱና ማሰቡ አይቀርም ።..መልካም አያያዝን አግኝቶ የማያድግ እንደሌለ ሁሉ በአያያዝ ጉድለትም እንዲሁ የማይበሰብስ ነገር የለም ። አጥብቀህ የያዝከው ነገር ከአንተ ጋር ይኖራል ፤ የለቀቅከው ደግሞ ሄዶ ይበሰብሳል " ይለናል ።

✻ተፈጸመ ✻

ምንጭ ጥበብ ከጲላጦስ ቅጽ ፩ ገጽ 40-44

ከፍልስፍና ዓለም እንዲሁም ንባብ ለሕይወት የቴሌግራም ቻናል ዝግጅት ክፍል ።

@filsfina @filsfina

@books4all32 @books4all32